የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

ETHIOPIAN PEOPLE PATRIOTIC FRONT

# ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የተሰጠ መግለጫ

ህዳር 10/2009 ዓ.ም

## ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተላለፈ ጥሪ

በሃገራችን ኢትዮጵያ የወያኔ ኢሃዴግ ዘረኛን መንግስት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነቅሎ ለመጣል እንደ መስቀል ችበ በአራቱም መአዘናት ተቀጣጥሎ የሚገኘው የነጻነት ትግል ቀና ብሎ መጓዝን አሃዱ በማለት ጀምሯል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ሰራዊት ባሳለፍነው ሳምንት ወስጥ በአደባይ፣በሃከር፣ ቀፍታና ሁመራ አካባቢ ከህዝብ ጠላትና ዘረኛ ስረዓት አራማጅ ከሆነው የወያኔ ኢሃዴግ ሰራዊት ጋር ባካሄደው ወጊያ በርካታ ድሎችን ማስመዝገቡና ወጤታማ የሆነበትን የአዲጎሽ ከተማን ህዝብ በማስባሰብ ትግሉን እንዲቀላቀሉ ጥሪ በማድረግ ምላሽ አግኝቷል።

ምንም እንኳን ሰራዊታችን ለጊዜው መሸጎበት የነበረውን ከፍታ ነጥብ ቦታ የወያኔ /ኢሃዴግ ሰራዊት በከባድ መሳሪያ እና በሂሊኮፕተር በመታገዝ የሰነዘረውን ድንገተኛ ጥቃት በመመከትና የአካባቢውን ህዝብ በማስተባበር የአጠፊታ እርምጃ ወስዷል።

በተጨማሪም በታችኛው አርማጭሆ ፣አብርሃጅራን ጨምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በተጓዘባቸው ቦታዎች የስረዓቱን አገልጋዮች በመቅጣት በገውላ እና ቀፍታ አጽመ-ሃርማዝ የሚገኘውን የወያኔን ሰራዊት በተለያዩ አቅጣጫዎች በመክበብ ከፍተኛ ውጊያ አካሂዷል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በተጓዘባቸው ስፍራዎች ከህዝቡ የተሰጠው ምላሽ እጅግ አስደሳችና የሃገር ፍቅር ስሜት የታየበት ታሪካዊና የማይረሳ ጊዜ ነበር።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

ETHIOPIAN PEOPLE PATRIOTIC FRONT

በተጨማሪም ከመሰል የአካባቢው ታጣቂዎችና ለነጻነት የሚታገሉ አጋሮቹ ጋር ኩታ ለኩታ በመቋጠር መጪውን ሳምንት ለተሻለ ስራ የተለያዩ ዕቅድችንም እያወጣ ይገኛል።

ስለሆነም በሌሎች ክልሎች የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ፣ የዚህን ግፈኛ ስረዓት ያለምትክ በማስቀረት የወደፊቷን ኢትዮጵያን ነጻና የሁሉም ዜጋ እኩል ምድር እንድትሆን የመታገያው ጊዜ አሁን ነው።

በመሆኑም ሃገሪን ፣ወገኔን የምትል የዚህ ዘመን አደራ ያለብህ ትውልድ ፣ የምትነሳበት ጊዜ አሁን ነው !! የሃገርን ጉዳይ ዘር፣ቀለም፣በታና ሃይማኖት አይለዩትም !! ዛሬ ነገ ሳትል ተነስ ፣ታጠቅ እኛን ወንድሞችህን ፣እህቶችህን ምሰል በማለት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን

አንድነት ሃይል ነው

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር